4127 Redwood Rd.
Oakland CA 94610
(510) 530-3681

No 2053/2013
Date 6.2.2013.

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## *"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ።" (1ኛ ጴጥ. 5፥2)*

**በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በዳላስ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ከግንቦት ፳፩ - ፳፫ ቀን ያደረገውን ፴፯ኛው መደበኛ ጉባዔ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ።**

<u>መግቢያ</u>

እንደሚታወቀው ቅዱስ ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ በመሆኑ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ሕይወትና ማንኛውም እንቅስቃሴ ውሳኔ ሰጪ የሆነ ሉዓላዊ አካል ነው። ስለሆነም ቅዱስ ሲኖዶስ በደመ ክርስቶስ የተዋጀውን የእግዚአብሔርን መንጋ ማለትም መላውን ማኅበረ ካህናትና ምእመናን በአግባቡ የመጠበቅና የመንከባከብ ከፍተኛ ኃላፊነትና አደራ አለበት። በዚህ አምላካዊ መርሕ መሠረት በስደት ላይ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ በያዝነው ሳምንት ለ፴፯ኛ ጊዜ ባካሔደው መደበኛ ጉባኤ በቀረቡት የመነጋገሪያ አጀንዳዎች ላይ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ውይይት አድርጓል። በመጨረሻም ጉባኤው ከዚህ የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥቷል።

፩ኛ/ በቅርቡ በአዲስ መልክ የተደራጀውንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ዕድገትና ውጤት ያስመዘገበው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት አገልግሎቱን ይበልጥ ለማስፋፋትና ለማጠናከር እንዲቻል በመዋቅሩ ሥር የተለያዩ መምሪያዎችን በማቋቋም እነሆ በስደት ዓለም የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ካለችበት ደረጃ ወደተሻለና ዘመኑን ወደዋጀ አሠራር እንድትሸጋገርና ለሕዝቡ ተደራሽነት እንዲኖራት ወስኗል።

፪ኛ/ ከዚህ ቀደም በተለያየ ምክንያት በገለልተኝነት ቆይተው የነበሩትንና በቅርቡ መሠረታዊ አቋማቸውን አስተካክለው ከቅዱስ ሲኖዶሱ ጋር አብረው ለመሥራት ራሳቸውን አዘጋጅተው የሚመጡ ወይም በአዲስ መልክ የሚቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናትን የንብረት ባለቤትነት አስመልክቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ፍጹም እንደተወረሰ ተደርጎ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመመለስና በየጊዜው የሚሰራጨውን የተሳሳተ አመለካከት ለማረም እንዲቻል ቅዱስ ሲኖዶስ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ንብረትነቱ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኑ ምእመናን መሆኑን በሚገባ ያረጋግጣል። ስለሆነም እስካሁን ድረስ በገለልተኝነት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የቅዱስ ሲኖዶሱን ጥሪ በአንድነት ተቀብለው፤ ለትውልድ የምትተላለፍ አንዲት፥ ቅድስት፥ ሐዋርያዊትና

ኵላዊት ቤተክርስቲያንን የሚጠቅም፤ እንዲሁም አገርንና ወገንን የሚጠቅምና የሚያኮራ ሥራ ለመሥራት ቅዱስ ሲኖዶሱን እንዲቀላቀሉ ሲል ጥሪውን ያቀርባል።

፫ኛ/ በአሁን ሰዓት በአገራችን ኢትዮጵያ ከየመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለው፤ ማደሪያ ያጡትንና በመንገላታት ላይ ያሉትን ውድ ወገኖቻችንን በጸሎት እንደሚያስባቸውና፤ ሕዝበ ክርስቲያኑም የዚህ ዐቢይ ችግር ሰለባ የሆኑትን ወገኖች ዘወትር በጸሎት እንዲያስባቸውና አቅሙ በሚችለው ሁሉ በጋራ እንዲራዳ ያሳስባል።

፬ኛ/ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አንድ ለማድረግ የተጀመረው ዕርቀ ሰላም እንዳይሳካና ይልቁንም ቀኖና ቤተክርስቲያን እየተፋለሰ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲቀጥል ዋነኛ ምክንያት የሆነው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ይህንን አድራጎት በአጽንዖት ይቃወማል፤ ይልቁንም መንግሥት እጁን ከቤተ ክርስቲያናችንና ከሌሎችም ሃይማኖታውያን ድርጅቶች ላይ እንዲያነሳም በጥብቅ ያሳስባል።

፭ኛ/ በአገራችን ለዘመናት ተከብረውና ታፍረው የኖሩት ታላላቅ ገዳማት መደፈርና በቅዱሳት መካናቱ ውስጥ በሚገኙት መናንያን ላይ የሚደረገውን ማናቸውም እንግልት በአጽንዖት ይቃወማል። መንግሥት ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ ሲገባው የችግሩ አካል በመሆን የሚያደርገውን ተጽዕኖ በአስቸኳይ እንዲያቆም ያሳስባል።

፮ኛ/ በአገራችን የሚገኙት ዜጎች የሃይማኖት ነጻነታቸውንና የሰብዓዊ መብት እንቅስቃሴዎቻቸውን በነጻነት ለማካሔድ በመጠየቃቸው፤ ሐሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው ምክንያት ያለ አግባብ የታሰሩት የኅሊና እስረኞች፥ እንዲሁም አሁን ጎልቶ የሚታየውንና በየቀኑ እየጨመረ የመጣውን የመንግሥትን ጫና እንዲሁም የሰብአዊ መብት ረገጣ አጥብቆ ይቃወማል። እስረኞችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ ።

፯ኛ/ ለሕዝባችን ነጻነትና አንድነት ቆመናል በማለት የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ሁሉ፤ ልዩነታቸውን አጥብበው በአንድነት ሆነው ነጻነት የናፈቀው ሕዝባችንን እንዲታደጉት ጥሪ ያቀርባል።

፰ኛ/ በዚህ በምንኖርበት በሀገረ አሜሪካ፤ በኦክላሆማ ግዛት በቅርቡ በተከሰተው የተፈጥሮ አደጋ ሰለባ የሆኑትን ወገኖችና መላው ቤተሰቦቻቸውን እግዚአብሔር አምላክ መጽናናትን እንዲሰጣቸውና ሕዝበ ክርስቲያኑም በጸሎት እንዲያስባቸው፤ የሚቻለውን ሁሉ እንዲተባበርም ይጠይቃል።

በመጨረሻም ይህን የቅዱስ ሲኖዶስ ዐቢይ ጉባዔ በመልካም ሁኔታ እንዲከናወን በማሰብ ጉልበታቸውን፤ ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ ላስተናገዱን በዳላስ የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቱድራል ማኅበረ ካህናት፤ ምእመናን፥ መዘምራንና የአስተዳደር አባላት ልባዊ ምስጋና በማቅረብ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አባታዊ ቡራኬና ጸሎት ጉባኤው ተፈጽሟል።

**ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ!**